# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 255 መጋቢት 26 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ!
አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

የሀገራችን ህዝብ ሆይ፡ ዛሬ ኢትዮጵያን ከገባችበት ዘረኛ መቀመቅ ስርአት ውስጥ የሚያወጣት ብቸኛ መፍትሄ፣ ፍርሃታችንን በጥሰን በተባበረ ጉልበትና ድፍረት ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ስናናግረው፣ ታግለን ስናስወግደው ብቻ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ኩራትና ክብርን፣ ተሳስቦና ተፈቃቅሮ፣ ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ጸጋን የምናመጣው። ስለሆነም በየትኛውም አቅጣጫ የሚደረገውን የነጻነት ጉዞ ትግል ትቀላቀሉ ዘንድ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በአማራ ተወላጆች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ አስመልክቶ መግለጫ አወጣ

የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ አካል ነዉ፣ በሚል ርእስ መግለጫ ያወጣ ሲሆን በመግለጫው ላይ እንዳሰፈረው ወያኔ በዚህ በያዝነዉ አመት ከመጋቢት ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአማራዉ ህዝብ ላይ አዲስና ሰፋ ያለ የጥቃት ዘመቻ መጀመሩን አውስቱአል፣ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በዚሁ መግለጫ ማጠቃለያው ላይ በአማራዉ ብሔረሰብ ላይ በማነጣጠር እየተፈጸመ ያለው የማፈናቀልና የማጥቃት እርምጃ በአገሪቱም ሆነ በአለም አቀፍ ህጎች ሁሉ በዘረኝነት ወንጀል የሚያስጠይቅ ከፍተኛ በደል ነው ብሎአል።

ይህ በንዲህ እንዳለ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ተፈናቅለው በፍኖተሰላም እና በባህርዳር ከተማ ያለመጠለያ ተበትነው የሚገኙ የአማራ ተወላጆች፣ ለዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባደሩ ሆድ አደር ባለስልጣናት አሁንም ግፍና በደል እየደረሰባቸው መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አመለከተ። የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከባህር ዳር ባስተላለፈልን በዚሁ ሪፖርት ላይ እንዳመለከተው እነኝህ ተፈናቃዮች እያቀረቡ ላለው ጥያቄ የክልል ባለስልጣናት ተብየዎች ምንም አይነት መፍትሄ ሊሰጡአቸው ባለመቻሉ ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸውንና ከዚህም አልፎ ከህዝብ እይታ ለመሰወር በሚል ራቅ ወዳለ ቦታ እንዲሰፍሩ መደረጋቸውን ገለጹአል።

ዘጋቢያችን እንደገለጠው እነኝኝህ በምእራብ ጎጃም ዞን በፍኖተሰላም ከተማ ሰፍረው የነበሩ ከ3 ሺ በላይ ተፈናቃዮች ከመሀል ከተማ እንዲወጡ ተደርገው፣ ጃቢ ጣህናን ወረዳ ውስጥ ባከል እየባለች በምትጠራ ገጠራማ ቀበሌ አንድ ጫካ ውስጥ እንዲሰፍሩ መገደዳቸውን ገልጹአል።

ህጻናት፣ እርጉዝ ሴቶች እና በሽተኞች ሳይቀሩ ቀን በጸሀይ፣ ሌሊት በብርድ እያንዳንዷን ቀን እንዲያስልፉ መገደዳቸውን የገለጠው ዘእጋቢያችን በመጀመሪያው ዙር ተፈናቅለው በባህርዳር ከተማ ከሚገኙት ተፈናቃዮች መካከል አንድ አርሶአደር የክልሉ ባለስልጣናት ጉዳዩ የክልል ስድስት ጉዳይ በመሆኑ ክልል ሶስት አያገባውም የሚል ምላሽ የሰጡአቸው መሆኑ ታውቁአል።

የመግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 4 ቀርቧል።

## የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናትን ተጠያቂ የሚያደርግ ምንም አይነት ስርአት አለመኖሩ ተረጋገጠ

የብአዴን ነባር ታጋይ ነው የሚባለው ህላዊ ዮሴፍ፣ ከፍተኛውን አመራር የምንጠይቅበት ስርአት የለም በማለት ሰሞኑን ብ አዴን ሲያካሂድ በነበረው ስብሳባ ላይ መናገሩን ዘጋቢያችን ከባህር ዳር በላከልን ሪፖርት ገለጠ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በዚሁ በብአዴኑ ስብሰባ ሙስና እና ፖለቲካ ብአዴንን እየፈተኑት እንደሆነ በግልጥ የታየ ሲሆን ህላዊ ዮሴፍ በንግግሩ ከፍተኛ አመራር አካላትን ተጠያቂ የሚያደርግ ስ ስር አት የለንም በማለት በዚሁ መድረክ መናገሩ ተሰብሳቢዎችን ሳይቀር እንዳስገረመ ገልጹአል። ህላዊ ዮሴፍ፣ የአማራ ልማት ማህበር ሊ/መንበር በነበረበት ጊዜ፣ የድርጅቱን የሂሳብ ሰነዶች አቃጥሎ ያለተጠያቂነት ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር መደረጉ አንዳንድ የብአዴን አባላትን ሲያብሰከስክ የቆየ መሆኑ ቢታወቅም ፣ በኢህአዴግ 9ኛው ጉባኤ ላይ ባሳየው ጠንካራ አቋምና ባቀረበው ንግግር ህሊናቸው የሚወቅሳቸውና ለሆድ ያደሩት የብአዴን አባላትን ማስደሰቱም ታውቁአል።

የባህርዳር ከተማ ህዝብ እና የብአዴን አባላት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እየፈጸመ ያለው ግፍና በደል ለከት ማጣት የውስጥ ለውስጥ ተቃውሞ ማስነሳቱ የሚታወቅ ቢሆንም በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ፣ ይህን እንቅስቃሴ ለማፈንና ለማዳከም የማይቆፍሩት ጉድጉአድ እንደሌለ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ የቀድሞ የብአዴን አባል መናገራቸውን ገልጹአል።

በረከትና አዲሱ ለገሰ ቁልፍና በአይነ ቁራኛም መከታተል የሚፈልጉአቸውን ግለሰቦች፣ ማለትም የክልሉን የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊ የነበረውን ከበደ ጫኔን እና የክልሉ የፍትህ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ዉስጥ መኖሪያ ቤቶችን ሆን ብላ ማቃጠል መጀመሩ ታወቀ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች መኖሪያ ቤቶችን ሆን ብሎ ማቃጠል መጀመሩን ቤታቸዉ የተቃጠለባቸዉ የከተማዋ ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዜና ገለጹ። ለዜጎች ምንም አይነት ክብርና ሀላፊነት የማየይሰማዉና የሚሰራቸዉን ስራዎች ሁሉ ሀይልና ተንኮል ቀላቅሎ የሚሰራዉ የወያኔ አገዛዝ አንድ ወር በማይሞላ ግዜ ዉስጥ አዲስ አበባ ዉስጥ ሦስት የመኖሪያ አካባቢዎችን አቃጥሎ በሰዉ ህይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ማድረሱ ታዉቋል። ቤታቸዉ የተቃጠለባቸዉና ሌሎችም ብዙ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እንደሚናገሩት ወያኔ ቤቶቹን የሚያቃጥለዉ እንደለመደዉ ቦታዉን ለህወሀት አባላትና ለቤተሰቦቻቸዉ ለመስጠት ነዉ ብለዉ ያምናሉ።

ባለፈዉ ረቡዕ መጋቢት 25 ቀን አዲስ አበባ ዉስጥ አባ ኮራን ሠፈር እየተባለ በሚጠራዉ አካባቢ ወያኔ ሆን ብሎ በጫረዉ እሳት ከ40 በላይ ቤቶች መዉደማቸዉንና በሁለት ሰዎች ላይ ከፍተኛ የመቃጠል አደጋ መድረሱን የአይን እማኞች ተናግረዋል። በዚሁ ዕለት በተመሳሳይ ሰዐት አውቶቡስ ተራ አካባቢ 32 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኙ ቤቶች ለሁለተኛ ጊዜ መቃጠላቸዉን ሁኔታዉን በቅርብ ሆነዉ የሚከታተሉት ዜና ምንጮች ገልጸዋል። አውቶቡስ ተራ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች ከዚህ ቀደም አካባቢውን ለቅቀዉ እንዲወጡ የተነገራቸዉ ቢሆንም ነዋሪዎቹ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ አካባቢዉ ሉለተኛ ገዜ ለእሳት አደጋ ተጋልጧል። ከሁለት ሳምንት በፊት በዚህ አካባቢ በደረሰው የእሳት አደጋ 11 ሰዎች መሞታቸው የሚታወስ ሲሆን የወያኔ መገናኛ ብዙሀን የሟቾች ቁጥር 8 መሆኑን መዘገባቸው ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእሳት አደጋዉ በደረሰባቸዉ አካባበዎች ሁሉ የእሳት አደጋ መኪናዎች ወደ ቦታዉ የሚድርሱት ቤቶቹ ተቃጠለዉ ካለቁ በሁዋላ መሆኑንና ከቦታው ከደረሱም በሁዋላም ውሀ የለንም እያሉ እንደሚመለሱ ለማወቅ ተችሏል። በወያኔ ድርጊትና በእሳት አደጋ ሰራተኖች ቸልተኛነት የተበሳጩ የአካባቢው ወጣቶች ሁለት የእሳት አደጋ መኪናዎችን በድንጋይ የሰባበሩ ሲሆን ከፌዴራል ፖሊስ ጋርም መጋጨታቸዉ ታዉቋል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ዘርን መሰረት ያደረገ ግጭት እንዲነሳ ግፊት እያደረገ ነው ተባለ

ዘረኛውና ለጥፋት የቆመው የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአማራ ተወላጆች ላይ እየተከተለ ያለው ፖሊሲ ወደ ዘር ግጭት ሊያስገባ እንደሚችል በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑ አንድ የዩኒቨርሲቲ ምሁር ለዝግጇት ክፍላችን በኢሜል በላኩት መል እክት ገለጡ። እኚሁ ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁን ምሁር እንደገለጡት የወያኔ አገዛዝ ከረጂም አመታት ጀምሮ በአማራው ህዝብ ላይ የነበረውን ቂምና ጥላቻ በተለያዩ ጊዚያቶችና በተለያዩ መንገዶች ዘግናኝ ጥፋቶችን ሲያደርስ የቆየ መሆኑ ሳያንሰው ሰሞኑን እየፈጸመ ያለው ድርጊት ደግሞ ችግሩን ወደተባባሰ ደረጃ የሚያደርስና የእርስ በርስ ግጭትም ሊያስነሳ እንደሚችል ያላቸውን ከፍተኛ ስጋት ገልጠዋል። ይህ የወያኔ ድርጊት አዲስ ነገር ሳይሆን ከሃያና ሰላሳ አመታት በፊት የነበረው እቅድ አካል ነው ያሉት እኚሁ ምሁር፣ ኢትዮጵያዊያን ሁኔታውን በንቃትና በጥንቃቄ መከተል ይገባቸዋል፣ የወያኔንም ተንኮልና መርዘኝነት በትንቃቄ ሊዋጉት ይገባል ብለዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከ5 እስከ 10 ሺ የሚደርሱ የአማራ ተወላጆች ከቤንሻንጉል ጉሙዝ አካባቢ ተፈናቅለው ወደ መጡበት የትውልድ ቀያቸው እንዲመለሱ መደረጉ የሚታወቅ ሲሆን ይህ የዘረኛ አገዛዝ ተግባርና ድርጊት ኢትዮጵያውያንን ማነጋገሩን ቀጥሏል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለኤቪዝን ኢሳት ያነጋገራቸው የተለያዩ የሲቪክ ተቋማት እና የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች እንዲሁም ታዋቂ ጋዜጠኞች ድርጊቱን በመኮንን ኢትዮጵያውያን በቃ ሊሉት እንደሚገባ እየመከሩ መሆናቸውን ዘግቧል።

ኢሳት እንደዘገበው በአገር ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ካሉት የሲቪክ ተቋማት መካከል የባለራእይ ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር የሆነው ወጣት ሀብታሙ አያሌው፣ የብሄር ፖለቲካ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያን ሊበታትናት እንደሚችል ገልጾ፣ በኢትዮጵያዊነት መልክና ቅርጽ የተፈጠረውን ዜጋ መልሶ በመነተት ወደ ጎሳ ቋጥኝ ማስገባት በልዩነት ላይ የተመሰረተ አስተዳደር መመስረት መሆኑን ተናግሯል። ወጣት ሀብታሙ የብሄር ፖለቲካው ችግር አገሪቱን ለመበታተን ይዳርጋታል በሚል ሲሰጥ የነበረው አስተያየት አሁን ፊት ለፊት እየመጣ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊነሳ ይገባዋል ማለቱን ገልጧል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ በአማራ ተወላጆች ላይ የጀመረውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ እንደቀጠለ ነው

ወያኔ ለአማራ ህዝብ፤ ባህልና ታሪክ ያለዉን ጥላቻ ከተራ ጥላቻ አልፎ በተግባር አማራዉን ወደ ማጥቃት ዘመቻ አደገ እንጂ ለአንድም ቀን ቀንሶ አያውቅም። አማራው እንደ ሰው ልጅ የመኖር መብቱ፣ ስብእናው ተገፎ ከቀየው፣ ከመንደሩ የአፈራውን ንብረትና ገንዘብ እየተቀማ መባረሩ፣ መሰደዱ፣ እንግልቱ ሁሉ የወያኔ የበቀል እርምጃ ነው።

በአሶሳ፤ በደኖና በአርባጉጉ ውስጥ አማራ በመሆናቸዉ ብቻ ህጻናት፤ሴቶችና አረጋዉያን በግፍ ተገድለዋል። ባለፈዉ አመት በደቡብ ክልል ጉራ ፈርዳ እየተባለ በሚጠራዉ አካባቢ ለረጂም አመታት ከአካባቢዉ ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ጋር ተግባብተዉ ይኖሩ የነበሩ የአማራ ብሄረሰብ አማራ በመሆናቸዉ ብቻ ለአመታት ያፈሩትን ንብረት ይዞ የመሄጃ ግዜ እንኳን ሳይሰጣቸዉ አከባቢዉን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለቅቀዉ እንዲወጡ እንዲፈናቀሉ ተደርጓል።

ከመጋቢት ወር መጀመሪያ ጀምሮ ወያኔ በአማራዉ ህዝብ ላይ አዲስና ሰፋ ያለ የጥቃት ዘመቻ ጀምሯል። በደቡቡ የአገራችን ክልል በጉራፈርዳ የጀመረዉን አማራውን ነጥሎ የማጥቃትና የማንገላታት ዘመቻ አሁን ደግሞ በሰሜን ምስራቅ የአገራችን ክፍል በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቀጥሏል።

የቅርብ ግዜው ደግሞ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ተፈናቅለው በምእራብ ጎጃም ዞን በፍኖተሰላም ከተማ ሜዳ ላይ ወድቀው የሚገኙት አማራ አርሶደአሮች የድረሱልን ጥሪ ማሰማታቸውና፤ ብሄረ አማራን እወክላለሁ ባዩ ብአዴን (የህወሃት ቡችላ) ጠበንጃ ደቅኖብን ወደ መጣችሁበት ተመለሱ ከዚህ ጥፉ ሲል አዋከበን፤ የወገን ያለህ ድረሱልን የት እንግባ ልጆቻችን የአውሬ ራት ሆኑ ሲሉ ስቃያቸውን አሰምተዋል። በርግጥ የህወሃት ተለጣፊው ብአዴን ሆዳቸው ስለሞላ ህሊናቸው ታውሮ ይህ በደል የሰው ልጅን የማጥፋት ሴራ መሆኑን እና በዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሚያስጠይቅ የተረዱ አይደሉም።

ሰሞኑን በቤንሻንጉል ጉሙዝ ለረጂም አመታት ከአካባቢዉ ህብረተሰብ ጋር ተቀላቅለው ይኖሩ የነበሩ አያሌ የአማራ ብሄረስብ ተወላጆች ያፈሩትን ንብረት ለመሰብሰብ እንኳን ግዜ ሳይሰጣቸዉ የኔ ብለው ከሚጠሩት የመኖሪያ ቦታቸዉ እንደባዳ እየተገፉ እንዲወጡ ሲደረጉ በአንጻሩ በባህርዳር ከተማ ብአዴን የቱባ ባለስልጣናቱን ከርስ ለመሙላት የክልሉን ህዝብ ጮኸት ጆሮ ዳባ ብሎ ሽርጉድ ሲል የነበረ መሆንን ያገናዘበ ኢትዮጵያዊ ቁጭት በርካታ ነው ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፡ እርግጥ ነው ይህን ዘረኛ ቡድን ለማስወገድ በሚደረገው መራራ ትግል ሂደት ውስጥ በደልና ሰቆቃው እየበዛ እንደሚሄድ ቢታወቅም ተባብረን ከታገልነው ግን ይህን ልናሳጥረው እንችላለን። አለበለዚያ ግን እስከ መቼ ነው ወገኖቻችን በትውልድ መንደራቸው የሀገር ውስጥ ጥገኛ ጠያቂ የሚሆኑት? የአማራ ብሄረሰብ ተወላጆች ከቀያቸው የተባረሩት በኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ነው።

ግንቦት 7 ንቅናቄ ይህ የወያኔ ስርአት እስካልተወገደ ድረስ በአማራው የተጀመረው ጭፍጨፋ፣ እንግልት፣ ስደት፣ መከራና ግድያ፤ ህወሃት በሌሎችም አጠናክሮ ይቀጥልበታል ብሎ ያምናል። ስለዚህ ምን እንጠብቃለን በወያኔ ያልተበደለ፣ ያልታሰረ፣ ያልተደበደበ፣ ያልተሰደደ፣ ያልተፈናቀለ፣ ያልተራበ፣ ያልተዋረደ፣ ያልተገደለ ህዝብ የለም። የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ጨካኝ ስርአት አማካኝነት በጨለማ ሂዎት ውስጥ እየኖረ ነው።

የሀገራችን ወጣት ሆይ፡ ወጣትነት ሀገር ተረካቢ፣ ባላደራ፣ ለውጥ ፈላጊ፣ ሀገሩን ጠባቂ ነው። ወገንህ ሲገረፍ ሲንገላታ ሲሰደድ ማየት እና ከንፈር መምጠት እሰከ መቼ ይሆን? ሰቆቃቸው፣ ቁስላቸው የድረሱልን ዋይታቸው መቼ ይሆን ተሰምቶን እንባቸውን በአለንላችሁ የወገን ደራሽነት የምንደርስላቸው? የምንጠርግላቸው? ግንቦት 7 ትግሉን የማቀጣጠያ ሰአት ጊዜው አሁን ነው ይላል። ወጣት፣ አዋቂ፣ ጎልማሳ፣ ሽማግሌ፣ ዘር ጾታ ቋንቋ ሳይለየን ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ምላሽ ስጡ፣ ተቀላቀሉ። በኢትዮጵያ የጠቆረውን ጨለማ በብርሃን መተኪያ ጊዜ ዛሬ ነው። ይህ ትውልድ የታሪክ ባለእዳ አይሁን።

በወያኔ ውስጥ ያላችሁ ይህ በደል ና ሰቆቃ የሚሰማችሁ ወገኖቻችን የውስጥ አርበኛ የምትሆኑበት ሰአት ላይ ናችሁ። ራሳችሁን እና ወገናችሁን ከቀን ጅብ ስርአት አድኑ። ከነጻነት ማግስት በኋላ ከሚመጣባችሁ ከየት ነበራችሁ ክስ ለመጽዳት ከነጻነት ታጋዮች ጋር አብሩ። ወያኔ ለ21 አመታት ህዝቡን ለማጋጨትና ለማባላት የሚያደርገው ስልት መሆኑን ተረድታችሁ የውስጥ ታጋዮች መሆናችሁን ማሳያ ጊዜው አሁን ነው። አሊያ ግን በአማራው ህዝብና በሌላው ማህበረሰብ ላይ እየተፈጸመ ባለው እጅግ አስከፊ ወንጀል በግልም ሆነ በቡድን፣ የንጹሀንን ደም እያፈሰሳችሁ ያላችሁ ወንጀለኞችና ተባባሪዎች ተብላችሁ፣ ከያላችሁበት ታድናችሁ ለፍርድ እንድትቀርቡ ንቅናቂያችን የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት በግልጽ እንድታውቁት ይገባል።

የሀገራችን ህዝብ ሆይ፡ ዛሬ ኢትዮጵያን ከገባችበት ዘረኛ መቀመቅ ስርአት ውስጥ የሚያወጣት ብቸኛ መፍትሄ፣ ፍርሃታችንን በጥሰን በተባበረ ጉልበትና ድፍረት ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ስናናግረው፣ ታግለን ስናስወግደው ብቻ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ኩራትና ክብርን፣ ተሳስቦና ተፈቃቅሮ፣ ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ጸጋን የምናመጣው። ስለሆነም በየትኛውም አቅጣጫ የሚደረገውን የነጻነት ጉዞ ትግል ትቀላቀሉ ዘንድ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጥሪውን በድጋሜ ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናትን ተጠያቂ የሚያደርግ . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

ቢሮ ሀላፊ የነበረውን ጌታቸው አምባየን ወደ ፌደራል መንግስቱ እንዲዛወሩ ያደረጉ ሲሆን ከበደ ጫኔን ከጸጥታ ዘርፍ ሃላፊነት ወደ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትርነት፣ ጌታቸውን ደግሞ ከፍትህ ቢሮ ሀላፊነት በምክትል ከንቲባነት ማእረግ የመሬት ባንክ ሃለፊ አድርገው ሾመዋል። እነኝሁ ሁለቱ ባለስልጣናት ወደ አዲስ አበባ እንደተዛወሩ በባህርዳር ከተማ ነዋሪ የሆነ ታዋቂው ባለሀብት ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ቤት ገዝቶ ቁልፉን ያስረከባቸው መሆኑን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል።

የነ በረከት ስምኦንን ስር የሰደደ የስለላና የጭካኔ ርምጃ በጥልቀት የሚያውቁት እኚሁ የቀድሞ ብ አዴን አባል ለዘጋቢያችን እንደገለጡት አንድ ሰው ስለ እነ በረከት ክፉ ቢያወራ በደቂቃዎች ውስጥ ራሱን እስር ቤት ውስጥ ያገኘዋል፣ ያሉ ሲሆን እሄው ስር የሰደደ ሆድ አደርነትና ፍራቻ በብ አዴን ወጣት አባላትም መባባሱንና እንዲያውም ወጣት አመራሮች ምንም ነገር ሳይናገሩ ጉባኤው መጠናቀቁን፣ ወጣት አመራሮች እንደ ተራው አባል ሁሉ "እናውቃለን፣ ብንናገር እናልቃለን " የሚሉ አይነት አቁአም ይዘዋል ብለዋል።

---

## የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ዉስጥ መኖሪያ ቤቶችን ሆን ብላ ማቃጠል መጀመሩ ታወቀ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች መኖሪያ ቤቶችን ሆን ብሎ ማቃጠል መጀመሩን ቤታቸዉ የተቃጠለባቸዉ የከተማዋ ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዜና ገለጹ።ለዜጎች ምንም አይነት ክብርና ሀላፊነት የማየይሰማዉና የሚሰራቸዉን ስራዎች ሁሉ ሀይልና ተንኮል ቀላቅሎ የሚሰራዉ የወያኔ አገዛዝ አንድ ወር በማይሞላ ግዜ ዉስጥ አዲስ አበባ ዉስጥ ሦስት የመኖሪያ አካባቢዎችን አቃጥሎ በሰዉ ህይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ማድረሱ ታዉቋል። ቤታቸዉ የተቃጠለባቸዉና ሌሎችም ብዙ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እንደሚናገሩት ወያኔ ቤቶቹን የሚያቃጥለዉ እንደለመደዉ ቦታዉን ለህወሀት አባላትና ለቤተሰቦቻቸዉ ለመስጠት ነዉ ብለዉ ያምናሉ።

ባለፈዉ ረቡዕ መጋቢት 25 ቀን አዲስ አበባ ዉስጥ አባ ኮራን ሠፈር እየተባለ በሚጠራዉ አካባቢ ወያኔ ሆን ብሎ በጫረዉ እሳት ከ40 በላይ ቤቶች መዉደማቸዉንና በሁለት ሰዎች ላይ ከፍተኛ የመቃጠል አደጋ መድረሱን የአይን እማኞች ተናግረዋል። በዚሁ ዕለት በተመሳሳይ ሰዐት አውቶቡስ ተራ አካባቢ 32 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኙ ቤቶች ለሁለተኛ ጊዜ መቃጠላቸዉን ሁኔታዉን በቅርብ ሆነዉ የሚከታተሉት ዜና ምንጮች ገልጸዋል። አውቶቡስ ተራ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች ከዚህ ቀደም አካባቢውን ለቅቀዉ እንዲወጡ የተነገራቸዉ ቢሆንም ነዋሪዎቹ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ አካባቢዉ ሉለተኛ ገዜ ለእሳት አደጋ ተጋልጧል። ከሁለት ሳምንት በፊት በዚህ አካባቢ በደረሰው የእሳት አደጋ 11 ሰዎች መሞታቸው የሚታወስ ሲሆን የወያኔ መገናኛ ብዙሀን የሟቾች ቁጥር 8 መሆኑን መዘገባቸው ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእሳት አደጋዉ በደረሰባቸዉ አካባበዎች ሁሉ የእሳት አደጋ መኪናዎች ወደ ቦታዉ የሚድርሱት ቤቶቹ ተቃጠለዉ ካለቁ በሁዋላ መሆኑንና ከቦታው ከደረሱም በሁዋላም ውሀ የለንም እያሉ እንደሚመለሱ ለማወቅ ተችሏል። በወያኔ ድርጊትና በእሳት አደጋ ሰራተኞች ቸልተኛነት የተበሳጩ የአካባቢው ወጣቶች ሁለት የእሳት አደጋ መኪናዎችን በድንጋይ የሰባበሩ ሲሆን ከፌዴራል ፖሊስ ጋርም መጋጨታቸዉ ታዉቋል።

# “አይቴ ብሔሩ ለአማራ . . . የአማራ አገሩ ወዴት ነው?” ኢትዮጵያ አይደለምን?

(በኤፍሬም እሸቴ)

በንግግርም ይሁን በጽሑፍ ለማንሣትም ሆነ ለመጥቀስ፣ ለመወያየትም ሆነ ለመከራከር ከማይመቹኝ (discomfort እንዲል ፈረንጅ) የኢትዮጵያ ርዕሰ ጉዳዮች ሁሉ ዘርን፣ ብሔረሰብን የተመለከተው ዋነኛውና አንዱ ነው። ጉዳዩ በዕለት ተዕለት የአገራችን ሕይወት ውስጥ ወሳኙ እና በሁነኛ መልክ ማኅበረሰባዊ ማንነታችንን እየበየነ እንዳለ እያወቅኹም እንዲህ እንደ አሁኑ በአደባባይ ለመውጣት ግን ብዙም አይቀለኝም። ምክንያቱ ሌላ ምንም ሳይሆን ጉዳዩ ያለው ስሱነት (sensitivity) ነው። አሁን ግን ላልፈው አልቻልኩም። አይገባምም። ለምን?

### መነሻ

ከአማራ ክልል ወደ ቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ ክልል ያሶ ወረዳ ተጉዘው የከተሙ በርካታ ሰዎች በወረዳው ባለሥልጣናትና ፖሊሶች፤ ሰብአዊ መብታቸው ተጥሶ ከቀያቸው መፈናቀላቸውን የሚያትት ዜና የሰሞኑ ኢትዮጵያውያን ድረ ገጾች/መገናኛዎች ዋነኛ ትኩረት ነው። ስለዚሁ ጉዳይ ዜና ያስነበበው “አዲስ አድማስ” ጋዜጣ ጉዳዩን በተመለከተ የሚከተሉትን ቁም ነገሮች አስፍሯል።

- በሚኖሩበት አካባቢ የእርሻ ቦታ በማጣታቸውና የተሻለ ሥራ ፍለጋ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ከአማራ ክልል ወደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ያሶ ወረዳ መሔዳቸውን፣
- “ከሌላ ቦታ እየመጣችሁና እየሠራችሁ የአካባቢውን ተወላጅ ሰነፍ አደረጋችሁት” በሚል ምክንያት ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ሳይሰበስቡ ከክልሉ እንዲወጡ መደረጋቸውን፣
- አንዳንዶቹ በያሶ ወረዳ ውስጥ የከተማ ነዋሪነትና የንግድ ፈቃድ በማውጣት ላለፉት ሰባት ዓመታት በሥራ ላይ መቆየታቸውን፣ ገሚሶቹ ደግሞ ከ1997 ጀምሮ የቀበሌው ነዋሪ በመሆን ከክልሉ ተወላጆች ጋር በስምምነት መሬት የእኩል እያረሱ የራሳቸውንም የባለመሬቱንም ሕይወት መቀየራቸውን፣
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማይ ዞን በያሶ ወረዳ ውስጥ በ**ሀሎ ትክሻ፣ ሆኒ፣ ሊጉ፣ ባብርኮ፣ ሻብቲ፣ ድልድል፣ ቲኒጆ መጢ**ና በመሰል ቀበሌዎች በግምት ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሺህ የሚጠጉ ከአማራ ክልል የመጡ ሰዎች እንደሚገኙበት፣
- “የክልሉ ነዋሪ ወዶንና ተቀብሎን በሰላም ነበር የምንኖረው” ማለታቸውን፣
- ጉጉታ በተባለ ቀበሌ ከአማራ ክልል የመጡ 43 ሰዎች እንዲሁም በሀሎ ሙከአርባ ቀበሌ የ25 ሰዎች መታወቂያ ተቀዳዶ ሲጣል መመልከታቸውን፣
- “እስከአሁን በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ከታሠሩት በርካታ ሰዎች በተጨማሪ በመኪና ተጭነው ነቀምትና ጊንቢ የተወሰዱት ሰዎች” መኖራቸውን፤ ስንቅ ሊያቀብሉ የሔዱ ሰዎችም መታሰራቸውን፤
- ወደመጡበት እንዲመለሱ የተወሰነው፤ በብአዴን፣ ኦህዴድ እና የኢሕአዴግ አጋር ፓርቲ በኾነው ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ ፓርቲ (ቤጉብዴፓ) በጋራ ተወያይተው በደረሱበት ውሳኔ መኾኑን ሥራው የወረዳው ብቻ ሳይሆን ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ በትስስር እየተሠራ መኾኑን የያሶ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ታደሰ ሻምበል ዳኛ መግለጻቸውን ዘግቧል።

ይህንን ዜና ከሌላ ተመሳሳይ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ጋር ካመሳከርነው ከደቡብ ክልል ጉራ ፈርዳ ወረዳ ከተፈናቀሉት/ እየተፈናቀሉ ካሉት ሌሎች ዜጎች ጉዳይ ጋር ልናነጻጽረው እንችላለን። ሁለቱንም አንድ የሚያደርጋቸው ደግሞ አማርኛ ተናጋሪዎች (አማሮች) መሆናቸው ነው።

### ሊወገዝ የሚገባው ተግባር

መነሻው ምንም ይሁን ምን፣ የክልሉ ፓርቲ ከማንም ጋር ይስማማ አይስማማ በነዚህ ዜጎች ላይ የተደረገው ተገቢነት የሌለው ነገር ነው። የዜጎች በአገራቸው ውስጥ የመዘዋወር፣ የመኖር መብት እንዲህ በጥቂት የፓርቲ ሹመኞች መወሰኑ የሚያስጨንቅም የሚያስደነግጥም ምልክት ነው። ከጉራ ፈርዳም ከቤንሻንጉል የተፈናቀሉት ሰዎች “አማሮች” መሆናቸው ደግሞ አጋጣሚ ነው ለማለት በጣም የዋህ (ሲገፉም ጅል) መሆን ይጠይቃል።

በቋንቋ ማንነት ላይ ብቻ በተመረኮዘው የአገራችን ፖለቲካ “አማራ” የሚባል ለብዙዎቹ “ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች” ጠላት የሆነ አካል እንዳለ በጓዳም በአደባባይም ሲነገር ብዙ ጊዜ ሰምተናል። ይህ ‘ፖለቲካ ያባውን - መፈናቀል ቢያወጣው’ (ሆድ ያባውን ... እንደሚባለው) ምንጩ የማይታወቅ የማይሆነውም ለዚህ ነው።

ከደቡብም ከቤንሻንጉልም ለመፈናቀል “አማራነቱ” ምክንያት የሚሆንበት ከሆነ “አይቴ ብሔሩ ለአማራ? ... የአማራ አገሩ የት ነው?” የትስ ሔዶ ይኑር? ኢትዮጵያ አገሩ አይደለምን?” ለማለት ያስገድደኛል። ደግሞስ አንድ ሰው አማርኛ ስለተናገረ የግድ ወደ አማራ ክልል መሔድ አለበት? ሁሉም ወደየክልሉ የሚለውን አዋጅ ያወጣውስ ማን ነው? አማርኛ የሚናገሩ ነገር ግን “የአማራ ክልል አገራቸው ያልሆኑ” ኢትዮጵያውያን የነገ ዕጣ ፈንታ ምንድር ነው?

### የመታወቂያ ነገር

ለረዥም ጊዜ የቀበሌ መታወቂያ ሳይኖረኝ እኖር ነበር። ከዕለታት በአንዱ ቀን ግን የግድ የቀበሌ መታወቂያ ማውጣት የሚያስፈልገኝ ጊዜ ደረሰና እኖርበት ወደነበረው ቀበሌ ሔድኩ። ፎርም ሞላኹ። ከዚያም መታወቂያው ላይ መስፈር ያለበት የብሔረሰብ (እነርሱ እንኳን ብሔር ነው ያሉት) ነገር ተነሣ። መናገር አልፈለኩም። ቀበልዬው ካልተናገርኩ እንደማይሰጠኝ እርግጥ አደረገው። መሞላት አለበት። የዘር ማንዘሬን “ደም” ሁሉ እስኪሰለቸው ደረደርኩለት። በምን ፎርሙላ እንደሆነ ባላውቅም እርሱ ደስ ያለውን አንዱን ቋንቋ ብቻ መርጦ ብሔሬን ሞላው። በመታወቂያዬ መሠረት ቀብልዬው የሞላው ክልልና ብሔር አባል ሆንኩ። መታወቂያ እየታየ ሰልፍ መያዝ ሲጀመር እኔም አቶ ቀበልዬው በሞላው ተርታ የግዴን ልገባ ነው ማለት ነው።

### ማንነትን በማወቅ ሰበብ ማንነትን ማጣት

ማንነትን ማወቅ፣ ባህልን መጠንቀቅ፣ ቋንቋን ጠብቆ መቆየት የሚደገፍ ብቻ ሳይሆን መብትም ነው። ነገር ግን አሁን ባለው መንገድ ድንበር እያጠሩ ሰውን ያለ ፍላጎቱ “ሰልፍህ በየት በኩል ነው?” የሚያስብል ብሔረሰባዊ አሰላለፍ ግን ጤናማ ካለመሆኑም በላይ አገር ብለን በጋራ የምንኖርባትን ጎጆ የሚያፈርስ ከፋፋይ አስተሳሰብ ነው። በተለይ እዚህ አሜሪካን አገር ከመጣኹ በኋላ ያየሁት እና እንኳን ቋንቋን ቀለምን ማለትም ነጭ፣ ጥቁር፣ እስያዊ፣ ሂስፓኒክ የሚለውን እንኳን ፎርም ላይ ለመሙላት የሰውየው ብቸኛ ፍላጎት መሆኑን ማወቄ በግዳቸው “ብሔረሰብ እንዲመርጡ” ለሚደረጉ ኢትዮጵያውያን እንዳዝንም፣ እንድቆጭም፣ እንድበሳጭም ያደርገኛል።

ዛሬ አማራ ተብለው እንዲወጡ የተደረጉት ዜጎች ሌላው ሰው “አማራ” ይላቸው ካልሆነ ምናልባት ራሳቸውን በቀበሌያቸውና በትውልድ ቀዬያቸው ከመጥራት የዘለለ ነገር የሚኖራቸው አይመስለኝም። እንዳሁኑ “አማራ ናችሁ” የሚለው አንድ ቃል ሳይጫንባቸው በፊት “አገራችን ጎጃም ነው” ወይም “መንዝ ነው” ይሉ ይሆናል። ኦሮሞውም “ሜታ ነኝ” ወይም “ቦረና ነኝ፣ ወለጋ ነኝ” ይል እንደሁ እንጂ እንደአሁኑ “ኦሮሞነት” አልተጫነበትም ነበር። ሌላውም ሌላውም። ማንነትህን እወቅ በማለት ሰበብ የተጫነበት የቋንቋ ቀንበር ከጎረቤቱ የሚለየውና አርሶ ከሚያድርበት ቀዬ የሚያፈናቅለው ከሆነ ማንነቱ እንደ ዕዳ ተቆጥሮበታል ማለት ነው።

ሌላው የሚያስጨንቀው ጉዳይ ምንነትን በማጠር ሰበብ ክፉ የፖለቲካ ጨዋታ የሚጫወቱ ቡድኖች መኖራቸው ነው። የዚህ ጨዋታ ግንባር ቀደሙ ደግሞ ኢሕአዴግ ራሱ መሆኑን መናገር አገራዊ ግዴታ እየሆነ ነው። ፓርቲው ለጊዜያዊ ፖለቲካዊ ጥቅም አገርን የሚያክል ትልቅ ቤት የሚያፈርስ ቁማር ውስጥ ነው ያለው። የሌሎች ብሔረሰቦችን ድጋፍ ለማግኘት አማራውን የመስዋዕት በግ አድርጎ የማቅረብ ቁማር። ዞሮ ተመልሶ ወደራስ ሊተኮስ (Backfire ሊያደርግ) የሚችል መድፍ መጫወቻ ማድረግ።

### መረጫጨት ተጀመረ?

አንድ ሰሞን ዝነኛ የነበረች ቀልድ “መረጫጨት ተጀመረ” ትል ነበር። የንስሐ አባት ጸበል ሲረጩ ለጨዋታ የመሰለው ትንሽ ነካ ያደረገው ሰው “መረጫጨት ተጀመረ?” ብሎ ውኃ ያነሳበት ታሪክ። በዚህ ዓይነቱ ከባድ ርዕስ ላይ ይኼ ቀልድ ስላቅ ሆኖ በውስጤ ብቅ አለ። ዛሬ ያባረሩ ሰዎች በሌላው ዘንድ “መረጫጨት ተጀመረ?” እንደማያሰኝባቸው ማወቅ ተስኗቸው ነውን? ምናልባትም ይህ እንዲሆን ፍላጎት እንዳላቸው ማን ያውቃል። እንደመንደር ጎረምሳ “ሰፈሬ ለምን መጣህ?” ሲሉ ሌላው በተራው እነርሱን “ሰፈሬ ለምን መጣችሁ?” እንዲላቸው ፈልገዋል ማለት ነው? ከዚያስ? ተጠቃሚው ማን ሊሆን? ወይስ ካርዱን የሚጫወተው ዋናው ሰውዬ ከኋላ ሆኖ እንዲስቅ? ኢትዮጵያችን እንደማትጠቀም በርግጠኝነት መናገር እችላለኹ።

### ለጊዜው

በእኔ ትንሽ ግምገማ ኢትዮጵያውያን በመታወቂያቸው እና በስማቸው እየተገማመቱ እንዲደባደቡ ትልቅ ፍላጎት አለ። እስካሁን ፍላጎቱ ያልተሳካው በኢትዮጵያውያን አርቆ አሳቢነት ነው። ይህንን የኢትዮጵያውያን አርቆ አሳቢነት በሕይወቱ ያልተረዳ እና በዚህ የዘር ፖለቲካ የተጠመቀ ትውልድ አገሪቱን እየተረከበ ሲመጣ እንዴት እንደምንሆን ግን እግዜር ይወቀው። ባለ ራእዩ ሰውዬ “አንተርሐሙዌ” (Interahamwe) ብለው ያሟረቱት ነገር ላለመድረሱ ማረጋገጫ የሚሰጥ ባገኘኹ በተደሰትኩ።

የቤንሻንጉል ክልል ሰዎችም ሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ለዚህ ዕብደት አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት አለባቸው። በዚህ ነገር መጠየቅ ሲመጣ ማዕከላዊው መንግሥትም “አልነበርኩበትም፣ የክልሉ ጉዳይ ነው” ማለት አይችልም። መሬት ለሕንዶች በነጻ በማከፋፈሉ ላይ እጁን የሚያስገባው የቤተ መንግሥት አካል ድሃ ገበሬዎች ሲፈናቀሉ የለኹበትም ሊለን አይችልም። የሚሰማውም አያገኝ።

መቼም የእምነት መሪዎቻችን ራሳቸውን ችለው ቆመው “ተዉ” ይላሉ ብለን አንጠብቃቸውም። እንዲህ ዓይነቱ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እንዲገታ መጠየቅ የሚገባቸው እነርሱ ቢሆኑም - በቅድሚያ። እነርሱ ባይናገሩም ሥልጣን ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ሐሳባቸውን መግለጽ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ነገሩ ወንጀል መሆኑን መናገር አለባቸው። “ትክክል አይደለም” ለማለት የግድ የአማራነት ቆብ መድፋት አያስፈልገንም። ሰብዓዊነት የሚሰማው በሙሉ ግድ ይለዋል። ለታሪክም ቢሆን። ከጊዜያዊ የፖለቲካ ወገንተኝነት ውጪ ማሰብ የሚያስፈልገው በዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ነው። የገዢው ፓርቲ ደጋፊና መሪ የሆኑትም ቢሆኑ ይህንን መቃወም ኢሕአዴግን መቃወም አድርገው መቁጠር አይገባቸውም። እንዲያውም ያስመሰግናቸዋል። ለኅሊናችንና ለልጅ ልጆቻችን ስለምናስረክባት ኢትዮጵያ ስንል “ኧረ በሕግ አምላክ፣ ኧረ በባንዲራው” እንበል።

## በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ አካል ነዉ!

**ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ መግለጫ**

**መጋቢት 2005 ዓ. ም**

የወያኔ መሪዎች እነ መለስ ዜናዊና ስብሐት ነጋ በ1967 ዓም ለትግል ደደቢት በረሀ እንዲገቡ ያነሳሳቸዉና ያሰባሰባቸዉ በአማራዉ ህዝብ ላይ ያላቸው ጥላቻና የበቀል ስሜት እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ በደልና እሮሮ አንገፍግፏቸዉ እንዳልሆነ በተለያዩ ግዜዎች ለህዝብ ይፋ የሆኑት የወያኔ መግለጫዎችና ለረጂም ግዜ ወያኔን የመሩት መለስ ዜናዊና ስብሐት ነጋ በየአደባባዩ ላይ ያደረጓቸዉ ንግግሮች በግልጽ ያሳያሉ። እነዚህ ከወጣትነት ግዜያቸዉ ጀምሮ በአማራ ህዝብ ላይ ጥርሳቸዉን የነከሱ የወያኔ መስራቾች በለስ ቀንቷቸዉ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላም ቢሆን ለአማራ ህዝብ፤ ባህልና ታሪክ ያለቻዉ ጥላቻ ከተራ ጥላቻ አልፎ በተግባር አማራዉን ወደ ማጥቃት ዘመቻ አደገ እንጂ ለአንድም ቀን ቀንሶ አያውቅም።

የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ያከበረዉ ወይም የኤኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅሙን ያስጠበቀለት ብሔረሰብ ባይኖርም በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን የወያኔ ዘረኞች የአማራን ህዝብ ከተቀሩት ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቹና እህቶቹ ነጥለዉ ለማጥቃትና የስነ ልቦና ዘይቤውን ለመስበር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በአጠቃላይ የወያኔ ዘረኛ ባለስልጣኖች አማራውን በተከታታይ ሲዘልፉ ቆይተዋል፤አዋርደው አስረዋል፤ ከአገር እንዲሰደድ አድረገዋል፤ አፈናቅለዋል ገድለዋል። ለምሳሌ ወያኔ ስልጣን በያዘባቸዉ በመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት ዉስጥ ብቻ አሶሳ፤ በደኖና አርባጉጉ ውስጥ አማራ በመሆናቸዉ ብቻ ህጻናት፤ሴቶችና አረጋዉያን በግፍ ተገድለዋል።

ባለፈዉ አመት በደቡብ ክልል ጉራ ፈርዳ እየተባለ በሚጠራዉ አካባቢ ለረጂም አመታት ከአካባቢዉ ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ጋር ተግባብተዉ ይኖሩ የነበሩ የአማራ ተወላጆች አማራ በመሆናቸዉ ብቻ ለአመታት ያፈሩትን ንብረት ይዞ የመሄጃ ግዜ እንኳን ሳይሰጣቸዉ አከባቢዉን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለቅቀዉ እንዲወጡና እንዲፈናቀሉ ተደርጓል። የወያኔ ባለስልጣኖችና በየአካባቢዉ የኮለኮሏቸዉ ምስለኔዎች አካባቢዉን በግድ እንዲለቅ የተደረገ ህግ አክባሪ ዜጋ የለም፤ የተባረሩት ህግ የጣሱ ግለሰቦች ብቻ ናቸው፣ በማለት አሳፋሪ ድርጊታቸዉን ለመደበቅ ሲሞክሩ ታይተዋል። ሆኖም ከጉራ ፈርዳና ከአካባቢዉ ተፈናቅለዉ ወደ መጣችሁበት አካባቢ ተመለሱ ተብለው በየሜዳው ያለምግብ፣ ውኃና፤መጠለያ የተበተኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የአማራ ተወላጆች ለወገኖቻቸውና ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ የድረሱልን ጩኸት ሲያሰሙ መሰንበታቸዉ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነዉ።

ወያኔ በዚህ በያዝነዉ አመት ከመጋቢት ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአማራዉ ህዝብ ላይ አዲስና ሰፋ ያለ የጥቃት ዘመቻ ጀምሯል። በደቡቡ የአገራችን ክልል በጉራፈርዳ የጀመረዉን አማራውን ነጥሎ የማጥቃትና የማንገላታት ዘመቻ አሁን ደግሞ በሰሜን ምስራቅ የአገራችን ክፍል በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቀጥሏል። ሰሞኑን በቤንሻንጉል ጉሙዝ ለረጂም አመታት ከአካባቢዉ ህብረተሰብ ጋር ተቀላቅለው ይኖሩ የነበሩ አያሌ የአማራ ተወላጆች ያፈሩትን ንብረት ለመሰብሰብ እንኳን ግዜ ሳይሰጣቸዉ የኔ ብለው ከሚጠሩት የመኖሪያ ቦታቸዉ እንደባዳ እየተገፉ እንዲወጡ ተደርገዋል። እዚህ ላይ አንድ እጅግ የሚያሳዝን ነገር ቢኖር በገዢዉ ፓርቲ ኢህአዴግ ዉስጥ አማራን እወክላለሁ ባዩ ብአዴን ወያኔ በአማራዉ ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን በደል ዝም ብሎ መመልከቱ ብቻ ሳይሆን ባለፈው አመት ከጉራ ፈርዳ ዘንድሮ ደግሞ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ እየተባረሩ እየወጡ ባሉ አማራዎች ላይ እየተፈጸመ ባለው ወንጀል ላይ ተባባሪ መሆኑን አሳይቷል።

ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ በአማራዉ ህዝብ ላይ ያደረሰውንና በማድረስ ላይ ያለውን ይህ ነዉ የማይባል ግፍና መከራ ከዚህ ቀደም እንዳደረገዉ ሁሉ አሁንም አጥብቆ ያወግዛል። ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ በዚህ በኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት የትግል ምእራፍ ውስጥ በደም የተቀባ፣ የቀለመ አኩሪ ታሪክ ያለውን የአማራውን ህዝብ መልሶ መላልሶ የሚያጠቃውና ይህንን ታላቅ ህዝብ ከየቦታዉ የሚያፈናቅለው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ከአማራዉ ህዝብ ጋር ብቻ በማያያዝ አገራችንን ለማዳከምና አንዱ ኢትዮጵያዊ በሌላዉ ኢትዮጵያዊ ላይ የሚደርሰዉን ግፍና መከራ "ምን አገባኝ" ብሎ እንዲመለከት ለማድረግ ባለው እጅግ አደገኛ ዕቅድ መሠረት መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲገነዘብ በጥብቅ ያሳስባል።

ከዚህም በተጨማሪ በአማራው ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ባለው እጅግ አስከፊ ወንጀል በግልም ሆነ በቡድን፣ የንጹሀንን ደም እያፈሰሳችሁ ያላችሁ ወንጀለኞችና ተባባሪዎች፣ ከያላችሁበት ታድናችሁ ለፍርድ እንድትቀርቡ ንቅናቂያችን የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት በግልጽ እንድታውቁት ይገባል።

በአማራው የደረሰው ጥቃት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ዜጎች ጥቃት ነው እንላለን። ግንቦት ሰባት ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም በግለሰብ ደረጃ የምንደሰትበትን ነጻነት የምናስጠብቀው በህብረት ነውና ወያኔ በአሁኑ ግዜ በአማራው ወገናችን ላይ የሚያደርሰውን ግፍ፤ መከራና መፈናቀል በእያንዳንዳችን ላይ እንደደረሰ በመቁጠር ይህንን ግፍ በመፈጸም የማይሰለቸውን ዘረኛ አገዛዝ በተባበረ ህዝባዊ ትግል ከአገራችን ለማስወገድ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ትግል ጥሪ ያስተላልፋል።

**ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣**
**መጋቢት 2005 ዓ. ም**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ዘርን መሰረት ያደረገ ግጭት እንዲነሳ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሌላው አስተያየት ሰጪ እውቁ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ መሆኑን የጠቀሰው ኢሳት፣ ተመስገን አማርኛ ተናጋሪዎች ከአብዛኛው ክልሎች እንዲወጡ መደረጋቸውን አስታውሷል። ካራቱሬን የመሳሰሉ ድርጅቶ ሀብት እንዲያፈሩ ሲፈቀድላቸው የኢትዮጵያ ዜጎች ግን ይህን መብት ተነፍጓቸዋል ። አደጋው ዛሬ የአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዜጋ ላይ የሚደርስ መሆኑን የገለጸው ጋዜጠኛ ተመስገን፣ ተፈናቃዮች ሰዎች በመሆናቸው ብቻ ፣ ነግ ለእኔ ተብሎ ድርጊቱ ሊወገዝ ይገባል ማለቱን ዘግቧል።

ከጉራ ፈርዳ የተፈናቀሉ አማርኛ ተናጋሪዎች ከ1 ሺ ገጽ በላይ ያለው ማስረጃ ለመለስ ዜናዊ አቅርበው እንደነበር ያስታወሰው ጋዜጠኛ ተመስገን፣ መለስ መልስ ሳይሰጥባቸው በመሞቱ እሱን የተኩትም በእጅ አዙር ተመሳሳይ ፖሊሲ እየተገበሩ መሆኑን ገልጿል ብሏል ኢሳት። ለሁሉም ድርጊት ህወሀት ተጠያቂ ነው የሚለው ጋዜጠኛ ተመስገን፣ የአማራውን ህዝብ እወክላለሁ የሚለው ብአዴንም ከተጠያቂነት እንደማያመልጥ መግለጡን ኢሳት ዘግቧል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org